## አዲሱ የኤሌክትሪፍ ታሪፍ ማስተካከያ

### 1. የታሪፍ ማሻሻያው አስፈላጊነት

- ከሁለት ዓመት በፊት መሻሻል የነበረበት የታሪፍ ማሻሻያ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ያልተሻሻለ መሆኑ፣
- የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማት ግብዓቶች ከዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚገዙ መሆኑና ከማከፋፈያ እስከ ማሰራጫት መስመሮች ድርስ ለሚከናወን የመልሶ ግንባታ ስራ የሚወጣውን ወጪ የማይሸፍንና ትክክለኛ ዋጋ የማያንፀባርቅ መሆኑ፣
- አሁን ያለው የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ለረዥም ጊዜ ያገለገሉና ያረጁ በመሆናቸው ከፍተኛ የመልሶ ግንባታ ሥራ የሚጠይቁ በመሆኑ የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ ገንዘብ ሚጠይቅ መሆኑ፣
- ሃይል ተጠቃሚ ደንበኞች የሃይል ፍላጎት መጨመርና እያደገ የመጣውን የሃይል ፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማት አለመኖር፣
- የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማት ግብዓቶች መግዣ ዋጋ መናር ለማሳያ ያህል በ2012 ዓ.ም 18.3 በመቶ፣ በ2013 ዓ.ም 21.8 በመቶ፣ 2014 ዓ.ም 34.7 በመቶ እንዲሁም 2015 ዓ.ም 32.9 በመቶ የገበያ ዋጋ እየጨመረ በመምጣቱ ተቋሙ በ2012 ዓ.ም ያስፈልገኛል ብሎ ከተነበየው የኢንቨስትመንት ወጪ ከ3.4 ቢሊየን ብር ወደ 5.5 ቢሊየን ብር ወጪ እንዲያወጣ አስገድዶታል፡፡ በተመሳሳይ በ2013 ዓ.ም ከ4.5 ቢሊየን ብር ወደ 6.4 ቢሊየን፣ በ2014 ዓ.ም ከ5.8 ወደ 7.7 ቢሊየን ብር ጭማሪ ታይቷል፡፡
- የውጪ ምንዛሪ መናር እና እንደልብ አለመገኘት ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የተቋሙ ግብዓት ከውጪ የሚያቀርብ መሆኑ፡- ለምሳሌ በ2013 ዓ.ም 39 ብር፣ በ2014 ዓ.ም 48.5 ብር፣ በ2015 ዓ.ም 53.3 ብር የውጪ ምንዛሪ እየጨመረ መምጣቱ በ2013 ዓ.ም ለመሰረተ ልማቱ ግንባታ ከ5 ቢሊዮን ወደ 7.7 ቢሊዮን የኢንቨስትመንት ወጪ እንዲወጣ ያስገደደ ሲሆን፤ ለዚህም ተቋሙ ያስፈልገኛል ብሎ ከያዘው 5 ቢሊዮን ብር ጋር ሲነጻፀር 2.7 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ በ2014 ዓ.ም ከ5.5 ቢሊዮን ብር ወደ 9.4 ቢሊየን ብር የኢንቨስትመንት ወጪ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡
- በአጠቃላይ ይህ የታሪፍ ክለሳ ጥናት ለአንድ ዓመት በሶስተኛ ወገን ባለሙያዎች ቡድንና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች ተጠንቶ ለነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ መጽደቁ፣

2. **የሃገራችን የኤሌክትሪክ ታሪፍ ከሳሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሃገራት ታሪፍ ጋር ሲነጻጸር**

- የሃገራችን የኤሌክትሪክ ታሪፍ ከሳሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሃገራት ታሪፍ ጋር ሲነጻጸር በጣም ርካሽና በጣም ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ ያህል አዲሱ የውጭ ምንዛሬ ከመተግበሩ በፊት ባለው የውጪ ምንዛሪ ምጣኔ በላይቤሪያ አማካኝ የአንድ ኪዋ ዋጋ በብር ሲሰላ-57 ብር፣ በሴራሊዮን 30 ብር፣ በቶጎ 29 ብር፣ በቤኒን 27 ብር፣ በጋቦን 24 ብር፣ በኬኒያ 17 ብር፣ ሱዳን 6 ብር እና በሃገራችን ኢትዮጵያ 5 ብር ገደማ እየተሸጠ ይገኛል።

3. **የታሪፍ ማሻሻያ ይዘት**

- አሁን ተግባራዊ የሚደረገው የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ የመኖሪያ ቤት፣ የንግድ፣ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ እንዲሁም የመንገድ መብራትን ታሪፍን ያካተተ ሲሆን የአገልሎት ክፍያ፣ የሃይል ፍጆታ ሂሳብ ክፍያ እና የከፍተኛ ሃይል ጭነትን ይጨምራል።

4. **የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያው የፀደቀበት ቀንና ያፀደቀው አካል**

- የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ በነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ባወጣው የኤሌክትሪክ ታሪፍ መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 008/2012 በ4 ዓመት አንዴ እንደሚሻሻል የሚያዝዝ ቢሆንም አሁን ተግባራዊ የሚደረገው የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ ጥናት የፀደቀው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 36ኛ መደበኛ ጉባኤ ነው።

5. **የታሪፍ አተገባበር ሂደት**

- አሁን ተግባራዊ የሚደረገው የታሪፍ ማሻሻያ ከመስከረም 2017 ዓ.ም ጀምሮ በየሩብ ዓመቱ ተከፋፍሎ ለ4 ተከታታይ ዓመታት ( እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ) ተግባራዊ የሚሆን ይሆናል።

6. **የታሪፍ ማሻሻያው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ደንበኞች እንዳይጎዳ ስለሚደረግ ድጎማ**

- ተግባራዊ የሚደረገው የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበትን እንዳያባብስ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ደንበኞችን የመክፈል አቅም ያገናዘበና ድጎማ የሚያደርግ ሲሆን፤ ጫናውን ለመቀነስ ደግሞ በየሩብ ዓመቱ ተከፋፍሎ የሚተገበር ነው፡ በዚህም ከ0 እስከ 200 ሜዋት/ሰ የሚጠቀሙ ደንበኞች የድጎማው ተጠቃሚ ናቸው።
- የኤሌክትሪክ ታሪፍን በየወቅቱ ከፋፍሎ በማስከፈል እንዴት የኑሩ ውድነትንና ጫና ማቃለል ይቻላል ለሚለው በምሳሌ ለማሳየት የሚከተለውን የሂሳብ ስሌት ይከተሉ **ወርሃዊ የኃይል ፍጆታ= በወር ውስጥ የተጠቀመው የፍጆታ መጠን በኪዋሰ* በዚያ እርከን ላይ ያለ የአንድ ኪዋሰ ታሪፍ ምጣኔ + የአገልግሎት ክፍያ**
- ለምሳሌ አንድ በወር 50 ኪዋት/ሰ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሆነ ደንበኛ ቀድሞ በነበረው ታሪፍ በኪ.ዋ.ሰ በወር ውስጥ (50*0.27+10) 24 ብር ብቻ ይከፍል የነበር ሲሆን አዲሱ ታሪፍ

በሚጀምርበት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ደግሞ (50*0.35+10.47)28 ይከፍላል፡፡ በተመሳሳይ በ2ኛው ሩብ ዓመት የአንድ ወር ክፍያው (50*0.43+10.71) 32 ብር ሲሆን፣ በ3ኛው ሩብ ዓመት (0.52*50+10.71) የአንድ ወር ክፍያው 37 ብር እንዲሁም በ4ኛው ሩብ ዓመት (0.60*50+10.95) 41 ብር ይከፍላል ማለት ነው፡፡

- በተመሳሳይ ደንበኛው በ2ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ በወር የሚከፍለው ትልቁ የኃይል ፍጆታ ሒሳብ 58፣ በ3ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ በወር 75፣ በ4ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ በወር 92 ብር ይከፍላል ማለት ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ማሳያ የሚያመለክተው ደንበኛው የተጠቀመው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ ታሪፍ በየሩብ ዓመቱ ተቀናንሶ ባይከፍል ኖሮ እና የአንድ ወር ወርሃዊ ፍጆታ ሒሳብ ዋጋ (በ4ኛው ዓመት የመጨረሻ ሩብ ዓመት የአንድ ኪዋስ) ቢሰላ የአንድ ወር የደንበኛው ወርሃዊ የፍጆታ ሒሳብ 92 ብር ይሆን ነበር፡፡ ይህም በ4 ዓመት ውስጥ የሚከፍለውን 8 ሺህ 812.80 ያደርሰው ነበር፡፡ ሆኖም ደንበኛው በየሩብ ዓመቱ የታሪፍ ፍጆታ መጠን ተከፋፍሎ እንዲከፍል ሲደረግ በ4 ዓመት ውስጥ የሚከፍለው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሒሳብ 1 ሺህ 477.96 ብር ይሆናል፡፡
- በተጨማሪም የታሪፍ ማሻሻያው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሕብረተሰብ ክፍሎችን ኑሮ እንዳይጎዳ ድጎማ በማድረግ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቅናሽ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲጠቀሙ የሚያስችልበትን አሠራር ዘርግቷል፡፡ የድጎማ ተጠቃሚ የሚሆኑት በወር ውስጥ እስከ 200 ኪዋስ የሚጠቀሙ ደንበኞች ሲሆኑ በዚህም ደንበኞች ታላቅ የዋጋ ቅናሽ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በወር ውስጥ ከ0 እስከ 50 ኪዋስ የሚጠቀሙ ድንበኞች ድጎማ ሳይደረግላቸው በትክክለኛው የታሪፍ ቀመር ቢሳላ 6.01 በኪዋስ መክፈል ቢኖርባቸውም ድጎማ በመደረጉ ወደ 0.98 ዝቅ ብሏል ወይም 84 በመቶ ድጎማ ተደርጎላቸዋል ማለት ነው፡፡
- በተመሳሳይ ከ51 እስከ 100 ኪዋስ ተጠቃሚ ለሆኑ ደንበኞች 61 በመቶ ድጎማ ተደርጎላቸው ከ6.01 ወደ 2.34 ዝቅ ብሏል፡፡ እንዲሁም ከ101 እስከ 200 ኪዋስ ለሚጠቀሙ ደንበኞች ደግሞ 35 በመቶ በመደጎም ከ6.01 ወደ 3.91 የታረፍ ዋጋ ተቀነሷል፡፡
- ድጎማ በመደረጉ የመጣ ውጤት ለምሳሌ በወር ውስጥ 50 ኪዋስ የሚጠቀም አንድ ደንበኛ ድጎማ ባይደረግለት ኖሮ ይከፍል የነበረው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሒሳብ 50*6.01+10.24 = 310.74 ብር ነበር፤ ሆኖም ድጎማ በመደረጉ 50*0.98+10.24 = 59.24 ይከፍላል ማለት ነው፡፡ ይህም 84 በመቶ ድጎማ በመደረጉ 252 ብረ ቅናሽ ተደርጎለታል ማለት ነው፡፡

## 7. የታሪፍ ማሻሻያው በመደረጉ ሊመጡ የሚችሉ ውጤቶች

- የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማት ግብዓቶችን በቀላሉና በበቂ ሁኔታ ለመግዛት ያስችላል፣
- አስተማማኝና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋል፣

- የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ለማስፋትና ቀጣይነት ያለው የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ እና የመልሶ ግንባታ ስራዎችን ለማከናን ያስችላል፣
- የተቋሙን ገቢ ለማሳደግ እና ተወዳዳሪ የሆነ ተቋም ለመፍጠር ይረዳል፣

8. **ደንበኞች በአጠቃቀም ወቅት ማድረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች**

- ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ የዋጋ ጫናን ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ፍጆታ አጠቃቀምን ማሻሻልና በቁጠባ መጠቀም፣
- ደንበኞች ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ እንዳይጨምርባቸው ሃይል ቆጣቢ የኤሌክትሪክ መገልገያ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣
- የሃይል ጭነት በማይበዛባቸው ስዓታት መጠቀም ከምሽቱ 4:00 እስከ ጠዋቱ 12:00 መጠቀም፣
- ያረጁ የኤሌክትሪክ መገልገያ ቁሳቁሶችን አለመጠቀምና በቂ ብርሃን ባለበት ቤት ውስጥ አንፑሎችን አለማብራት እና ሌሎችንም ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልጋል፣

9. **የታሪፍ ማሻሻያው ዝርዝር አተገባበር**

## ሰንጠረዥ ሀ1. የፀደቀ የችርቻሮ ኢነርጂ ታሪፍ እና አተገባበር

| ተ.ቁ | ኢነርጂ ታሪፍ | መለኪያ | በስራ ላይ ያለው ታሪፍ | 2024/25 | | | | 2025/26 | | | | 2026/27 | | | | 2027/28 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | |
| | | | | 1ኛ (3ኛ ወር) | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | የመኖሪያ ቤት | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | 0 — 50 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 0.27 | 0.35 | 0.43 | 0.52 | 0.60 | 0.68 | 0.76 | 0.84 | 0.92 | 1.00 | 1.08 | 1.16 | 1.24 | 1.32 | 1.40 | 1.48 | 1.56 |
| 1.2 | 51 — 100 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 0.77 | 0.95 | 1.13 | 1.31 | 1.49 | 1.67 | 1.85 | 2.03 | 2.21 | 2.39 | 2.57 | 2.76 | 2.94 | 3.12 | 3.30 | 3.48 | 3.66 |
| 1.3 | 101 — 200 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 1.63 | 1.89 | 2.15 | 2.41 | 2.67 | 2.93 | 3.19 | 3.45 | 3.72 | 3.98 | 4.24 | 4.50 | 4.76 | 5.02 | 5.28 | 5.55 | 5.81 |
| 1.4 | 201 — 300 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 2.00 | 2.46 | 2.92 | 3.38 | 3.84 | 4.30 | 4.76 | 5.22 | 5.68 | 6.14 | 6.60 | 7.06 | 7.52 | 7.98 | 8.44 | 8.89 | 9.35 |
| 1.5 | 301 — 400 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 2.20 | 2.66 | 3.12 | 3.57 | 4.03 | 4.49 | 4.95 | 5.41 | 5.86 | 6.32 | 6.78 | 7.24 | 7.70 | 8.15 | 8.61 | 9.07 | 9.53 |
| 1.6 | 401 — 500 ኪዋሰ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 2.41 | 2.85 | 3.29 | 3.73 | 4.17 | 4.62 | 5.06 | 5.50 | 5.94 | 6.39 | 6.83 | 7.27 | 7.71 | 8.16 | 8.60 | 9.04 | 9.48 |
| 1.7 | ከ500 ኪዋሰ በላይ | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 2.48 | 2.92 | 3.35 | 3.79 | 4.23 | 4.66 | 5.10 | 5.54 | 5.97 | 6.41 | 6.84 | 7.28 | 7.72 | 8.15 | 8.59 | 9.03 | 9.46 |
| 2 | የንግድ (አጠቃላይ) | ብር /ኪ..ዋ.ሰ | 2.12 | 2.61 | 3.09 | 3.57 | 4.05 | 4.53 | 5.01 | 5.50 | 5.98 | 6.46 | 6.94 | 7.42 | 7.90 | 8.39 | 8.87 | 9.35 | 9.83 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አነስተኛ ኢንደስትሪ | ብር /ኪ.ዋ.ሰ | 1.53 | 1.76 | 2.02 | 2.29 | 2.56 | 2.82 | 3.09 | 3.36 | 3.62 | 3.88 | 4.15 | 4.41 | 4.68 | 4.93 | 5.20 | 5.46 | 5.73 |
| 4 | መካከለኛ ኢነደስትሪ | ብር /ኪ.ዋ.ሰ | 1.19 | 1.39 | 1.61 | 1.83 | 2.05 | 2.27 | 2.49 | 2.71 | 2.94 | 3.16 | 3.38 | 3.60 | 3.82 | 4.04 | 4.26 | 4.48 | 4.70 |
| 5 | የመንገድ መብራት | ብር /ኪ.ዋ.ሰ | 2.12 | 0.35 | 0.43 | 0.52 | 0.60 | 0.68 | 0.76 | 0.84 | 0.92 | 1.00 | 1.08 | 1.16 | 1.24 | 1.32 | 1.40 | 1.48 | 1.56 |

## ሰንጠረዥ ሀ2. የኢነርጂ ችርቻሮ የአገልግሎት ታሪፍ

| ተ.ቁ | አገልግሎት ታሪፍ | መለኪያ | በስራ ላይ ያለው ታሪፍ | 2024/25 | | | | 2025/26 | | | | 2026/27 | | | | 2027/28 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | | ሩብ አመት | | | |
| | | | | 1ኛ (3ኛ ወር) | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ (3ኛ ወር) | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ (3ኛ ወር) | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 1ኛ (3ኛ ወር) | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | የመኖሪያ ቤት | ብር /# | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9.1 | ድህረ ክፍያ | ብር /# | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9.1.1 | እስከ 50 ኪ.ዋሰ | ብር /# | 10.00 | 10.24 | 10.47 | 10.71 | 10.95 | 11.19 | 11.42 | 11.66 | 11.90 | 12.14 | 12.37 | 12.61 | 12.85 | 13.08 | 13.32 | 13.56 | 13.80 |
| 9.1.2 | ከ 50 ኪ.ዋሰ በላይ | ብር /# | 42.00 | 42.95 | 43.90 | 44.85 | 45.80 | 46.75 | 47.70 | 48.65 | 49.60 | 50.55 | 51.50 | 52.45 | 53.40 | 54.35 | 55.30 | 56.25 | 57.20 |
| 9.2 | ቅድመ ክፍያ | ብር /# | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 9.2.1 | እስከ 50 ኪ.ዋሰ | ብር /# | 3.50 | 3.67 | 3.84 | 4.01 | 4.18 | 4.36 | 4.53 | 4.70 | 4.87 | 5.04 | 5.21 | 5.38 | 5.55 | 5.72 | 5.89 | 6.07 | 6.24 |
| 9.2.2 | ከ 50 ኪ.ዋሰ በላይ | ብር /# | 14.70 | 15.02 | | | | | | | | | | | | | 19.13 | 19.45 | 19.77 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 15.33 | 15.65 | 15.97 | 16.28 | 16.60 | 16.92 | 17.23 | 17.55 | 17.87 | 18.18 | 18.50 | 18.82 | | | |
| 10 | የንግድ (አጠቃላይ) | ብር /# | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 10.1 | ድህረ ክፍያ | ብር /# | 54.00 | 55.19 | 56.38 | 57.57 | 58.75 | 59.94 | 61.13 | 62.32 | 63.51 | 64.70 | 65.89 | 67.07 | 68.26 | 69.45 | 70.64 | 71.83 | 73.02 |
| 10.2 | ቅድመ ክፍያ | ብር /# | 18.90 | 19.31 | 19.71 | 20.12 | 20.53 | 20.94 | 21.34 | 21.75 | 22.16 | 22.57 | 22.97 | 23.38 | 23.79 | 24.19 | 24.60 | 25.01 | 25.42 |
| 11 | አነስተኛ ኢንደስትሪ | ብር /# | 54.00 | 55.19 | 56.38 | 57.57 | 58.75 | 59.94 | 61.13 | 62.32 | 63.51 | 64.70 | 65.89 | 67.07 | 68.26 | 69.45 | 70.64 | 71.83 | 73.02 |
| 12 | መካከለኛ ኢነደስትሪ | ብር /# | 54.00 | 55.19 | 56.38 | 57.57 | 58.75 | 59.94 | 61.13 | 62.32 | 63.51 | 64.70 | 65.89 | 67.07 | 68.26 | 69.45 | 70.64 | 71.83 | 73.02 |
| 13 | የመንገድ መብራት | ብር /# | 54.00 | 55.19 | 56.38 | 57.57 | 58.75 | 59.94 | 61.13 | 62.32 | 63.51 | 64.70 | 65.89 | 67.07 | 68.26 | 69.45 | 70.64 | 71.83 | 73.02 |